የነ ፋሌቅ ወጥመድ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com

ሰኔ ፳፻፬ ዓ.ም.

መግቢያ

ኢትዮጵያን ለማፈራረስ፡ ቤተ ክርስቲያናችንን ለመደምሰስ ገብረ ኪዳን ደስታና ስብሀት ነጋ የዘረጉትን የጥፋት ወጥመድ፤ የአቶ መለስ መንግስት ለ፳ አመታት በመጠቀም ሲፈጽመው የኖረውን የጥፋት ዘመቻ፤ በዋልድባ ገዳም ለማጠናቀቅ አሁን በመጣደፍ ላይ ነው። ዶክተር አረጋዊ በርሄ በመጽሐፋቸው እንደገለጹት፡ ይህ መንግስት ከዛሬ ፳ አመታት በፊት ያቀደውን የጥፋት ዘመቻ እንዴት እንደ ጀምረውና በማጠናቀቅ ላይም መሆንን "የነ ፋሌቅ ወጥመድ" በሚል ርእስ ባዘጋጀኋት በዚህች ጦማር ለማሳየት እሞክራለሁ። ለማንበብ ትእግስቱን፡ ለመረዳት ማስተዋሉን፡ የተረዳነውን ወደተግባር ለመለወጥ ጥበቡን እግዚአብሔር ያድለንና፤ ጣማሯ "ወጥመድ አስፈንጣሪዋ ቆቅ" በሚል መግቢያ ተጀመራ፡ ከዚህ በታች ሰፍረው በሚታዩ ት በአምስት አናቅጽ ተከፍላ በመዘጋጅት ቀርባለች።

- ፩ኛ አጥማጆች እነማን ናቸው?
- ፪ኛ ወጥመዱ ምን ነበር?
- ፫ኛ ወጥመዱ አለቃን እንዴት ጠለፋቸው?
- ፬ኛ በዘመናችን ለመተርጎም አስቸጋሪ የሆኑ ጥቅሶች
- ፭ኛ ግራ ቀኝ የሚያዩ ሩቅ የሚያስቡ ወጥመድ አስፈንጣሪ ቆቆች እንደነበሩት አባቶች እንሁን

ወጥመድ አስፈንጣሪዋ ቆቅ

ቆቆ ትንሽ ፍጥረት ናት። ላለመጠመድ በቀኝ በግራ በፊት በኋላ በሩቅና በቅርብ ያለውን ሁሉ በመፈተሽ አንገቷን አስረዝማ ትቃኛለች። አዘውትራ ባንድ እግሯ በመቆምም ታስባለች። በልዩ ዘዴ ወጥመዱ ካልተሸፈነባት በቀር በቀላሉ አትጠመድም። እንዲያውም ወጥመዱን ታስፈነጥረዋለች። በተጠመደ ወጥመድ የሚጠመደው በአካል የገዘፈው ያልነቃ ጅግራ ነው። ከጅግራዋ የባሰም በሆዱ እየተመራ ገደል የሚገባ ትልቅ ዛቀኛ በሬ አለ። ቆቅ መጠኗ እጅግ ትንሽ ስትሆን ሊታረድበት በፊቱ የሚሳልበትን ቢለዋ ማየት ከማይችለው ከግዙፉ በሬ ይልቅ ይህን ያህል መርቀቋ ታስደነቃለች። በሬን የራሱ ሆድ ስፋትና አልጠገብ ባይነቱ አንጣቆ (ዋሻጣ) ይገለዋል። ከበረቱ ወጥቶ የሚዛቅ ግብስብስ ሲፈልግ የጅብ መንጋ ይበለዋል ወይም ገደል ይገባል። **“በሬ ሆይ! ገደል ትገባለህ ግብስብስ ስታይ”** የሚባለውም በዚህ ምክንያት ነው።

ሊቃውንት አባቶቻችን ህብረተሰብን ለማገልገል ወደ ክህነቱ የሚመጡትን ቅኔ እንዲማሩ ተጽዕኖ የሚደርጉት፡ ራስን ለማዳን የቆቅ ንቁህነት፡ ሌላውን መርዞ ለመግደል የእባብ ንቁህነት፤ ጥበብ የመቅሰም ችሎታ ያላቸውን በአንህብት: በሽታ የሚያሰራጩን ዝንቦች ሌሎችን ሁሉ አስደናቂ ፍጥረታት እየፈለጉ ሰም አድርገው ወርቁን በማልበስ፤ ወርቁን የበለጠ እንዲያሸበርቅ የማድረግ ችሎታ ኖሯቸው የቅዳሴውን የኪዳኑን የሊጦኑን ምሥጢር በመገንዘብ የዚህን ሁሉ ፈጣሪ በግብራቸው በቃላቸው መግለጽ እንዲችሉ ነበር።

እውነተኞች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልጆች በቅኔ ትምህርት ፍጥረታትን ዳሰው ጭንቅላታቸው ሲተባ ወደ መጽሐፍ ትርጓሜ ይሻገራሉ። በዚህ ተቀርጸው የወጡ ካህናት (ሰዎች) በማንኛውም ወጥመድ የማይገቡ ወጥመድ አስፈንጣሪ ቆቆች ናቸው። ቆቅ በዚህ አልጠመድ ባይ ባህርይዋ ለነቃ ሰው መገለጫ ሆናለች። “እገሌ ቆቅ ነው፥ ወይም እገሊት ቆቅ ናት” ይባላል። <u>የጥንት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ስለ ቤተ ክርስቲያናቸውና ስለታላቋ ኢትዮጵያ አገራቸው ሩቅ የሚያስቡ ወጥመድ አስፈንጣሪ ቆቆች ነበሩ</u>።

ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያንና ቤተ ክርስቲያናችንን ከገቡበት ወጥመድ ማውጣት ይህን ያህል ዘመን የፈጀብን የዛቀኛው በሬ፡ ያጋሰሱ ፈረስ፡ ወይም የጅግራዋ ባህርይ ያላቸው ሰዎች ቁጥር፤ የወጥመድ አስፈንጣሪዋ ቆቅ ባህርይ ካላቸው ሰዎች ቁጥር እጅግ ከመጠን በላይ በመብዛቱ ነው። ለመሆኑ ቆቅ ሆነን ነቅተን ማየት የተሳነን፡ ማስፈንጠር ያቃተን ወጥመድ ምንድ ነው? አጥማጆችስ እነማን ናቸው?

፭ኛ. አጥማጆች እነማን ናቸው?

ከላይ እንደገለጽኩት በባህላችን ሰውን ለማክበር ለማወደስና ለመርገም ወይም ለመንቀፍ በተፈጥሮ ገጸ ባህርይ እንጅ ሰው በትከለ ሰውነቱ፡ ወይም በዘሩ አይነቀፍም አይወደስም። በዚህ ግንዛቤ በየዘመናቱ የሚከሰቱትን የአጥማጆችን ስም በቀጥታ ከመጥቀስ ይልቅ ቀደም ብሎ የተፈጸመ የነሱን ባህርይ ገላጭ የሆነ ታሪክ ወይም ፍጥረት መጥቀስ ነው። የነዚህን አጥማጆች ባህርያት የሚገልጹ ብዙ ነገሮች እንዳሉ

የታወቀ ነው። እርቄ ሳልሄድ የግእዙ ቋንቅ አፍላቂዎች በቅኔ ችሎታቸው ያካባቢያቸውን የተፈጥሮ ባህር ዋኝተው ያቋረጡ፡ ከአድማስ ባሻገር ያለውን ለማያት እንደ ቆቅ ክሳደ-አዕምሯቸውን የሚመዙ መምህራን በቅኔያቸው በትርጓሜያቸው ሲናገሩ የሰማሁትን መንደርደረያ አደርጋለሁ።

እሱም "ወለኤቦር ተወልዱ ሎቱ ክልኤቱ ደቂቅ ስሙ ለአሐዱ ፋሌቅ እስመ በመዋዕሊሁ ተከፍለት ምድር፡ ወስመ እኁሁ ዮቅጣን"(ኦሪት፲፡፳፭) የሚለው ነው። ከኖሕ የጥፋት ዘመን በኋላ ምድር ከፋፋይ የሆኑ ሁለት ሰዎች ተወለዱ። አንደኛው **ፋሌቅ** ሁለተኛው **ዮቅጣን** ይባላል። ከሁለቱ አንዱ ፋሌቅ የተባለበት ምክንያት በሱ ዘመን መሬት ስለተከፋፈለች ነው ይላል። *(በነገራችን ላይ "ፈለቀ" ማለት ከፈለ ማለት ነው። 'ለ' ላልታ መነበብ አለባት። 'ለ' ተረግጣ ከተነበበች ትርጉሟ ከከፈለነት ወደ መነጨነት ይለወጣል)*ሊቃውንት አበው "ፋሌቅ እስመ በመዋዕሊሁ ተከፍለት ምድር" እንዲል ብለው ለግስነቷ መነሻ አርገው እንደ ማስረጃ ይጠቅሱታል።

መሬትን ከፋፍሎ ህዝብን መበትን የሁለቱም*(ፋሌቅና ዮቅጣን)* ወንድማማቾች የጋራ ክፉ ጠባይ ቢሆንም፡ ከዮቅጣን ይልቅ፡ ፋሌቅ በመሬት መክፈል ላይ አጥብቆ ስለሰራ ለመክፈሉ የታሪክ ትዝታ ይሆን ዘንድ ፋሌቅ ተባለ። በዘመናችንም አገራችንን ኢትዮጵያን ለመክፈል ሁለት ወንድማማቾች ኢትዮጵያውያን ዳግማውያን ፋሌቅና ዮቅጣና ተወልደዋል።

ክፉና መልካም በተፈጥሮ ውበትና ክፋት ባህርይ ይገለጻል እንዳልኩት፤ በባህላችን የተጸውኦም ሆነ የተቀብኦ ስም አካባቢውን ዘመኑንና የተደረገውን የሚያስታውስ ስም ለልጅ ይሰጣል። ቃሉ ደስ ይላል ላንደበትም ይመቻል ተብሎ ሲወለድ በአካባቢው የተፈጸመውን ታሪክ የማያንጸባርቅ ስም ለልጅ አይሰጥም። ንብረት ያዘረፈውን አገር ያስወሰደውን፥ ህዝብ እንዲበታተን ያደረገውን መለሰ ወይም አንድአርጌ፡ በዘረጋው ወጥመድ ህብረተ ሰብ ወደ ጨላማ እየጎተ ሚከተውንና ሰውን ሁሉ በማስመረር ላይ ያለውን ስብሀት ነጋ፤ አገር ያስካደውን፡ ህዝብ ያሳዘነውን፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ ወጥመድ የዘረጋውን ገብረ ኪዳን ደስታ የሚል ስም የሚሰይም ኅብረተ ሰብ አዕምሮውን የሳተ ነው።

በዚህ ኢትዮጵያዊ ባህላችን መሰረት ከዚህ ቀደም የዲሲ ቅድስት ማርያም ካህን ያውም ርዕሰ ደብር ብሎ ራሱን የሰየመው አስመሳይ ደፍተራ በጠለሰመው የክህደት መጽሀፉ ላይ የሴቶችን ክብረ ንጽህና "ገለፈት" በማለቱ ለፈጸመው ትልቅ ክህደት መታሰቢያ ይሆነው ዘንድ ስሙን "ደፍተራ ገለፈት" ብለን እንደሰየምነው፤ በዘማንችንም ኢትዮጵያን ከፋፍለው ህዝቡን የበተኑትን ወንድማማቾች አንዱን ዮቅጣን፡ በኢትዮጵያ እምብርት ላይ ቆሞ ኢትዮጵያ እንድትከፋፈል ጠንክሮ የሰራውን ደግሞ ፋሌቅ ብለነዋል። ይህ የዘመናችን ኢትዮጵያዊው ፋሌቅ አገር የከፋፈለበትን ህዝብ ያቆራረጠበትን ሰይፍ በመዘርጋት ብቻ ላይ አላቆመም። ሰውን እንደ አሳ የሚያሰግር መረብ: እንደ ጅግራ የሚያጠምድ ወጥመድ ተብትቦ በመዘርጋቱ ከፋሌቅ ይልቅ እጅግ የከፋ ፋሌቅ ነው። በተለያዩ መንገዶች እየተጠለፉ ያለፉት እነ አለቃ አያሌው እነ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ይህን ከላይ የተገለጸውን ታሪካዊ ንጽጽር በህይወት ኑረው ቢሰሙት ኖሮ: ሀሳባቸውን ሲገልጹበት በኖሩት መወድስ ይበልታቸውን ባስተጋቡ ነበር። አሁን ወደ ጥመዱ እሻገራለሁ።

፪ኛ. ወጥመዱ ምን ነበር? እንዴትስ ተሰራ?

ወልዶ ያሳደጋቸውን የትግራይን ሕብረተ ሰብ፡ እትብታቸው የተቀበረበትን የትግራይን ምድር እግዚአብሄር ይባርክና፤ ዶክተር አረጋዊ በርሔ "A Political History of the Tigray people's Liberation Front (1975-1991)**" በሚል ርእስ ለ**Doctoral dissertation (page 300) **ወይም** **ባሳተሙት** **መጽሀፋቸው** (page 246) **ላይ የወጥመዱን ምንነት፡ ማን ሰርቶ እንዳጠመደውና ለምን እንደተጠመደ እንዲህ ሲሉ በመግለጽ አስተምረውናል።**

"Thirdly, the TPLF launched a series of conferences or 'seminars' for selected parish priests in 1979 to win them over The underling motive of the seminars was to isolate the church in Tigrai from the wider Ethiopian church in order to foster Tigrian nationalism along the line of the TPLF's strategic objective. Suppressed Tigrian nationalism was invoked to challenge the dominant Ethiopian Orthodox Church. The initial woreda seminars for priests were conducted by an eloquent TPLF fighter, Gebre Kidan Desta., a graduate of The Theological College at Addis Ababa University The themes of the seminar were to replace the Ethiopian Church's authority by a TPLF- minded church and the language in the church with Tigrigna and, ultimately to further Tigrian nationalism and identity.

This process involved the mobilization of parish priests and ordinary Christians to isolate them from the church's national hierarchy. To weaken church authority, an intelligence group was formed under Sibhat Nega to infiltrate the well-established monasteries in Tigrai such as Debre Damo, by planting TPLF members camouflaged as monks and influencing church activities in the interests of the TPLF. .

In 1987 and 1989, regional and national conferences for priests were organized by the TPLF in the liberated territories to reshape the Tigrai church in line with the TPLF programme."

A separate secretariat of the Orthodox Church was formed in the liberated areas of Tigrai and was supposed to operate under the TPLF guidelines. Practically, the Ethiopian Church was divided in to two separate secretariats, one under the regime and the other under TPLF. Both worked in Tigrai until 1990, when the TPLF overran Meqele, the capital of Tigrai. The regime's secretariat fled Meqele for Dessie and the secretariat in the liberated territories entered Meqele and operated until the TPLF seized power in1991."

ወደ አማሪኛ ሲተረጎም

የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ሰፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሰሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው።

*የወረዳ ሰልጠና የተጀመረው በጠንካራ ትግሉ የታወቀው ካዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በነገረ መለኮት ትምህርት የተመረቀው **ገብረ ኪዳን ደሰታ** ነው። የሰልጠናውም ይዘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጠቅላላ መዋቅራዊ አስተዳደር በትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ባለሟሎች መተካትና በቤተ ክርስቲያኒቱ አካባቢ የትግርኛ ቋንቋ እንዲሰፍን ማድረግ ነው።*

በዚህ መንፈስ ተቀረጸ የተዘረጋው እቅድ በየሰበካውና አጥቢያው ያሉትን ቄሶችና ምእመናኑን ቤተ ክርስቲያኒቱ ጠብቃ ካቆየችው ታሪክና ብሄራዊ መዋቅር እየገነጠሉ በመስኮብለል ወደ ነጻ አውጭው አምባ መሰብሰብ ነው። መነኮሳት በመምሰል ደብረ ዳሞ ወደ መሳለሉት ገዳማት ሰርጎ በመግባት የድርጅቱን እቅድ በማስተጋባት የሚያዳክም አጥኝ ኃይል በስብሀት ነጋ መሪነት ተመሰረተ። የማሰልጠኑ ተግባር ከተፈጸመ በኋላ፤ የሰለጠኑት አስመሳይ መነኮሳት በትግራይ ምድር ዙሪያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ከዋናው ጽፈት ቤት መገንጠልን በ1987 እና በ1989 ተግባራዊ እንዲያደርጉት አደረገ።

ከነጻ አውጭው አመራር የሚቀበለው መነኮሳት እየመሰለ ሰርጎ የገባው አስመሳይ ቡድን፡ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና መዋቅር ተገንጥሎ ከነጻ አውጭው ጋራ ጎን ለጎን የማካሄ ሰራውን ቢሮ ከፍቶ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ከዋናው ጽ ቤትና ከነጻ አውጭው ትእዛዝ በሚቀበሉት ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት በግልጽ መታየት ጀመረ። እስከ 1990 ድረስ ሁለቱም ጎን ለጎን ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ፤ ነጻ አውጭው መቀሌን ሲቆጣጠር፡ ከዋናው ጽ ቤት አመራር ይቀበል የነበረው መቀሌን ለቆ በ1991 ወደ ደሴ ሲሄድ፡ በነጻ አውጭው ሰር ይመራ የነበረው ቡድን መቀሌውን እንዳለ ተረክቦ ተቆጣጠረ”

ዶክተር አረጋዊ በርሔ ከዚህ በላይ የገለጹት ኢትዮጵያ ስለተከፋፈለችበት ሰይፍና፡ ቤተ ክርስቲያናችን ስለተጠመደችበት ወጥመድ ነው። ይህ ሰይፍ በትግራይ ቀጥቃጮች መልክና ቅርጽ እንዲይዝ ይደረግ እንጅ፡ ተበይዶ የተሰራው በጣሊያኖች ነው። ወጥመዱ የተሰራበት ሽቦም በነ አቶ ፋሌቅ በትግራይ ምድር ላይ ቢገጣጠምም፡ የመጣው ዛሬ በህይወት ከሌሉት ከነሳዳም እና ከነ ጋዳፊ ነው። የተሰራው ወጥመድ በትግራይ አካባቢ መጀመሪያ ተዘረጋ። ስራውን የጀመረው በትግራይ አካባቢ

ባሉት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ላይ ነው። የሚስማማቸውን እያጠመዱ ወደ አጥማጅነት መለወጥ ነው። ለባህርያቸው የማይስማማውን መግደል ወይም እንደ ማይፈለግ አሳ ከባህሩ (ከህብረተ ሰቡ) አውጥቶ መጣል ነው። በዚህ ወጥመድ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ብዙዎች ተጠምደውበታል። ዶክተር አረጋዊ እንደገለጹልን መጀመሪያ የተጠመዱትና ለዚህ ስራ ተመልምለው የገቡት የትግራይ አካባቢ ሰዎችና መነኮሳት ከሆኑ፤ አነቡነ ማትያስና [አቡነ ጢሞቴወስ ደጋግመው እንደነገሩንና የሚያደርጉትንም ስንታዘብ የመጀመሪያው ዋናው ተጠላፊና ለጠላፊነትም የተመለመሉት አቡነ ጳውሎስ ናቸው ቢባል ሊያስተባብል የሚችል ማነው? [ከአቡነ ማትያስ ጋር የተደረገውን ቃለ-ምልልስ እዚህ ላይ በመጫን ያዳምጡ፤ ወይም ከሌሎች ጳጳሳት ጋር የተደረገውን ቃለ-ምልልስ እዚህ ላይ በመጫን ያዳምጡ]:: በዚህ ከተስማማን በነ አቡነ ጳውሎስ ከተጠመዱት ውስጥ አንዱ ነፍሳቸውን ይማርና አለቃ አያሌው ታምሩ ነበሩ። እንዴት እንደጠለፋቸው እንየው።

፫ኛ. ወጥመዱ አለቃ አያሌው ታምሩን እንዴት ጠለፋቸው?

“በጠንካራ ትግሉ የታወቀው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በነገረ መለኮት ትምህርት የተመረቀው” እያሉ ዶክተር አረጋዊ የገለጹት፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን አዳክሞ፤ ኢትዮጵያን መከፋፈል የሚያስችል ተንኮል ፈጥሮ ማስተማር የጀመረው ገብረ ኪዳን ደስታ የተባለው ሰው ነው። ከድንጋይ የተሰራው ሀውልታቸው እንዳይፈርስ ታግለው እስካሁን ያቆዩት አቡነ ጳውሎስ፡ አገር ድንበር ሲፈርስ፡ ነገረ መለኮት ሲጣስ ዝም ያሉት፡ በነዚህና በሌሎች ሁሉ ማስረጃዎቻችን በገብረ ኪዳን ደስታ ተንኮል የተጠለፉና ሌላውን ለመጥለፍ የሰለጠኑ ነዎ ብንላቸው አይደለሁም ለማለት ከልብ አድርቅነት ውጭ ምን አንደበት አላቸው? በዚህ ወጥመዳቸው የተጠለፈው ብዙ ቢሆኑም አቡነ ጳውሎስ በመጀመሪያ የጠለፏቸው አለቃ አያሌው ናቸው።

የአለቃ አያሌው ሙያ የቅኔ መምህርነት ነው። የቅኔ ችሎታቸውን መሰረት በማድረግ ሀሳብ አፍሶ የመናገር ከፍተኛ ችሎታ ነበራቸው። አለቃ እንደ ቅኔ ዘረፋ ሀሳቦችን እያሰበሰቡ ዘርፈው የመናገር ችሎታቸው የላቀና፡ ቆቆ መሳይ ባህርይ ቢኖራቸውም፡ ቀን የጎደለባት ቆቅ አልፎ አልፎ እንደምትጠመድ ቆቅ ሆነው በነ አቡነ ጳውሎስ ተጠመዱ።

የንግግር ችሎታቸውና ለአገር ፍቅር የነበራቸውን ጥንካሬ እንደ ምሳሌ ልንወስደው ቢገባም፤ በሃይማኖቱ ግን መጀመሪያ በገዛ ራሳቸው እልህ ይመስላል ሰውን ሁሉ ገደል ከተውታል። በዚህም ዙሪያ የሚጽፍ ሁሉ የአለቃን የታሪክ ተወቃሽነት ድርሻ ሳይጠቁም ቢያልፍ ራስን በወጥመድ ውስጥ መክተት ይሆናል እላለሁ።።

እነ ፋሌቅ (መለሰ) ኢትዮጵያን ማጥፋት ከቻሉባቸው ሁለት ዋና ዋና መንገዶች ተሰሚነት ያላቸውን የአገር ሽማግሌዎችንና መንፈሳዊንት፡ እውቀት፡ ሞራልና ብሄራዊ ታማኝነት ያላቸውን የሀይማኖት አባቶች ማጥፋት፡ ማዳከም፡ ታሪክን መሰረዝና ድንበር ማፋለስ ነው:: ለዚህ ዕቅዳቸው መሳካት የሚጠቀሙበት የተንኮል ዘዴ አስቀድመው የሰውን ደከማ ጎን በስለላ ማጥናት ነው:: ይህንን

የረቀቀ ተንኮል ያልተረዱትን አለቃ አያሌውን በማበሳጨትና፥ በቁጣቸውም የተሳሳተ እርምጃ እንዲወስዱ በመገፋፋት ከወጥመዳቸው ውስጥ እንዲገቡ አድርገዋቸዋል:: አለቃ አያሌው የወሰዱትን የተቃውሞ እርምጃም ለራሳቸው (ለነ መለሰ) በሚጠቅም መንገድ እየለወጡ ለተመልካች አቅርበውታል። አለቃ "አቡነ ጳውሎስ ሃይማኖታቸውን ክደዋል ካቶሊክ ናቸው" ብለው በተሳሳተ መስመር እርቀው ሄደዋል። በፖለቲካዊ ቀመር ሊሚጓዙት አቡነ ጳውሎስን በመጨረሻ የሚጎዳቸው ቢሆንም፤ አለቃ አያሌው በእልክ እየተገፉ "አቡነ ጳውሎስ ካቶሊክ ናቸውና በሳቸው እንዳትባረኩ እንዳትቆርቡ" ብለው በአቡነ ጳውሎስ ላይ ያሳለፉት ኢ-ኦርቶዶክሳዊ ውግዘት እምነቱን ለይቶ ባልተረዳው ህዝብ በሰፊው ተስተጋብቷል፤ ይሁን እንጅ በመላ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትና በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የአለቃን ክስና በአለቃ አነሳሽነት ያተስተጋባው ህዝባዊ ጩኸት ተደማጭነት አላገኘም። ይልቁንም በተቃራኒው አቡነ ጳውሎስ የሚሰነዘርባቸውን ሁሉ እውነተኛ ክስና ወቀሳ ያለቃ አያሌውን የተሳሳተ ክስ እያለበሱ እንዲያቀርቡ ረድቷቸዋል።

ከነ ፋሌቅ ጋራ ተባብረው ለሚያራምዱት ፖለቲካቸው መጋረጃ ይሆንላቸው ዘንድ እርስ በርሳችን ተለያይተን እንድንፋጅ ህዝቡን ለመከፋፈል እነ ፋሌቅ ከፈጠሩት ፖሊሲ ጋራ የአለቃ አያሌውን ስህተት ደምረው፡ ለውስጥ ፖለቲካቸውም ሳይቀር ተጠቅመውበታል።

አቡነ ጳውሎስ እውነተኛ የሃይማኖት ሰው ቢሆኑ ኑሮ፤ አለቃ አያሌው የተወገዱበትን ምክንያት ለህዝብ ገልጸው፤ ይህም ማለት አለቃ በተከታታይ ባሳተሟቸው መጻህፍቶቻቸው የገለጹትን የተዋህዶውን ነገረ መለኮት ሰርዘው፡ ከኦርቶዶክሱ ነገረ መለኮት ውጭ የሆነ ትምህርት ስላሰራጩ ከሊቃውንት ጉባዔ ሊቀመንበርነታቸው አስወግጃቸዋለሁ ብለው፡ በአለቃ የገባውንም ስህተት አውግዘውና በጥንቱ ኦርቶዶክሳዊው ግንዛቤ እንዲታረም አድርገው ለህዝብ ግልጽ ማድረግ በተገባቸው ነበር። ነገር ግን አለቃ አያሌውን ያስወገዱበትን ምክንያት ግልጽ ሳያደርጉ፡ አለቃን ካባረሩ በኋላ የገባውን ስህተት አላረሙትም። ይልቁንም የገባውን ስህተት ለሌላው ማጥመጃ አድርገው ተጠቀሙበት። ያለቃን ማስወገድም እሳቸውን ለመቃወም ለሚነሳው ሁሉ እንደመቀጣጫ አድርገውታል።

ለምሳሌ:- አለቃን ካባረሩ በኋላ በሳቸው የገባውን ስህተት በማቀፍ የማህበረ ቅዱሳን ልጆች በዚህ ጉዳይ ሰውን ሁሉ አወገዝን እያሉ እንዲበጠብጡ፡ እነሱም እንዲጠሉበት አድርገው ተጠቅመውበታል። በዚህ ጉዳይ ለሰባት ዓመታት ሲያፋጁን ከቆዩ በኋላ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ በስህተት በመጓዝ ላይ ያለውን ይህንኑ ማህበር ለመምታትና አባ ሰረቀን ለመታደግ ሲሉ ከዛሬ ሰባት ዓመታት በፊት ያቀረብነውን ሀሳብ ትክክል እንደሆነና አባ ሰረቀም ይህን በማቅረባቸው እንዳልተሳሳቱ በማዘዣ እንዲገለጽላቸው አደረጉ። ማህበሩ በዚህ ጉዳይ አባ ሰረቀ እንዲወገዙለት ያደረገው ግፊት እምነቱ ገብቶት ሳይሆን በጠላፊ ተጠላፊነት ስላደረገው ባይመሰገንበትም፡ በአባ ሰረቀ ላይ ያካሄደው ግፊት የአቡነ ጳውሎስን አጥማጅነት የማህበሩን ተጠማጅነት በግልጽ የሚያሳይ ሆኗል።

አለቃ በእልክ ከስህተት እንደገቡ ሁሉ ማህበረ ቅዱሳን የሚባለው ድርጅትም በሀሳብ የማይስማማውን አንዳንድ ሰው ለማጥቃት በየዋህነት በሚያደርገው እንቅስቃሴ፡ ከዛሬ ሰባት ዓመታት በፊት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ሰባዊነቷን አረጋግጠን ስህተቱን ገልጸን በላክነው ማሳሰቢያ ላይ አባ ሰረቀ ፈርመው ስለነበረ፡ መጥለፊያ አድርገው አቀረቡባቸው። አባ ሰረቀም ራሳቸውን ለመከላከል ባደረጉት ትግል "እውነትና ንጋት" በሚል ርእስ ካቡነ ማትያስ ጋራ የተጻጻፍነውን እንዳለ አወጡት። እውነተኛ መንፈሳዊ የሊቃውንት ጉባኤ ቢኖር ኖሮ፤ አቡነ ማትያስና አቡነ ጳውሎስ ከቤተ ክርስቲያናችን በተባረሩ ነበር። ምክንያቱም አቡነ ጳውሎስ የካህናቱ ጉባኤ "ባስቸኳይ ካልተስተካከለ በቤተ ክርስቲያናች መከፋፈል የሚያስከትል መሆኑን ጠቁሞ የላከላቸውን ማሳሰቢያ ለሰባት ዓመታት አፍነው ኖረው ዛሬ"

በሃይማኖት ማንም እየተነሳ ማንንም ማውገዝ አይችልም ከሚለው ቃላቸው ጋራ፡ አባ ሰረቀን ነጻ ናቸው የሚል ደብዳቤ ቤተ ክህነቱ እንዲጻፍ ማድረጋቸው ትልቅ አድላዊነትና ከሳቸው የማይጠበቅ ሽፍጥ ነው። ጽሁፉን ተመልከት ይሁን እንጅ በዚህ ጉዳይ በውስጥና በውጭ ለሰባት ዓመታት በሀሰት ስትከሰስበትና ሲዘመትባት የነበረችው የከንሳስ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሄርን እጹብ ሥራ እያደነቀች፡ ተደብቆ የነበረው ክህደትና ሽፍጥ በይፋ እንዲወጣ ላደረጉት ለ አባ ሰረቀ ተገቢ ምስጋናቸውን ሳትለግስ አታልፍም።

ማህበረ ቅዱሳን የተባለው ድርጅት አውቆም ይሁን ሳያውቅ ከነፋሌቅ ወጥመድ ውስጥ ገብቶ በወጥመዱ ሌላውን በመጥለፍ ብዙ ዘመን አሳልፏል። የከንሳስ መድኃኔ ዓለምን አፍነውና እንዳትንቀሳቀስ አድርገውበት የነበረውን ወጥመድ፡ በጦማሮቻችን ሁሉ ደጋግመን ገለጽነውልና እራሳቸው አቡነ ጳውሎስ ገልጸው እንደጻፉት ማህበረ ቅዱሳን ያውቃል። የሁሉንም ነፍሳት ይማርና፤ አለቃ አያሌው ያወገዟቸው መጋቤ ብሉይ ሰይፈንም የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ እንዳደረጓቸው ማህበረ ቅዱሳን ያውቃል። (መጋቤ ብሉይ ሰይፈን በተመለከተ ከዚህች ጦማር በኋል የማቀርበው አለኝ) ይህን ሁሉ ሽፍጥ ማህበረ ቅዱሳን እያወቀ፤ አቡነ ጳውሎስን ቅዱስ አባታችን እያለ ሲከተልና ሊላውን ሲያሳድድ የኖረው ለምን ይሆን? ይህን ባህርይ መለስ ብለን ስናጤነው ማህበረ ቅዱሳን አውቆም ሆነ ሳያውቅ በገብረ ኪዳን እኩይ ስልጠና አልተጠለፈበትም ማለት ይቻላልን?

አቡነ ጳውሎስ "መሀርዎሙ ለእለ የሐውሩ ዘእንበለ አእምሮ፡ ወለእለ ተምህሩ አጽንእዎሙ፡ ወሚጥዎሙ ለስሁታን ወንግርዎሙ በኩሉ ጊዜ በእንተ ስህተቶሙ"(ፍ. አን ፩ ቁ ፻፲፯) ማለትም "ያለመረዳት በጨለማ የሚሄዱትን በትእግስት በርህራሄ ሳትሰለቹ ከተሳሳቱበት መንገድ መልሳችሁ ትክክለኛውን መንገዱ አሳዩአቸው። ተምረው የተረዱትን በተረዱበት እውነት ጸንተው እንዲቆሙ አበርቷቸው" የሚለውን ለመፈጸም ነበር ከቦታው የተቀመጡት። አቡነ ጳውሎስ ግን በተቃራኒው ይህን ሊፈጽሙ ይቅርና ማህበረ ቅዱሳን በተጓዘበት ስህተት በህወት የሌሉትንና ያሉትን አርቶዶክሳውያንን ሰዎች ስም ዝርዝር እያቀረበ ይወገዙ ሲል፡ ለሁለት እኩይ ተግባሮቻቸው ሲሉ ማህበረ ቅዱሳን መልካም እንዳደረገ ዝም በለው ለቀቁት።

አንዱ እኩይ ተግባራቸው የወጣቱ ሃይል አንድ ቀን አይኑን ከፍቶ የኦርቶዶክሱን ነገረ መለኮት ሲረዳ በአገር ላይ የሚደርሰውንም ሲገነዘብ፡ በነሱ ላይ መነሳቱን የማይቀር መሆኑን ስለሚረዱ ወጣቱ በገባበት ወጥመድ በፈጸመው ስህተት መልሰው ለመምታት እንዲመቻቸው ሲሆን ። ሁለተኛው ደግሞ ማህበረ ቅዱሳኖች በፈጸሙት ስህተት የታዘበውና የሰለቸው ህብረተ ሰብም "ማህበረ ቅዱሳኖች እጅግ አብዘተውት ነበር፡ እንኳን አሏቸው" ብሎ ህዝብ እንዲፈርድባቸውና ከህዝብ ለይተው ለመምታት ሲሉ የዘረጉት ተግባራቸው ነው።

አቡነ ጳውሎስ ወጣቱ በስህተት እየተነዳ ነው ሲሏቸው ዝም፤ ህዝበ ክርስቲያን ታረደ ሲሏቸው ዝም፤ ሃይማኖቱ ተዛባ ሲሏቸው ዝም። ገዳማት ተቃጠሉ ሲሏቸው ዝም፤ የዋልባ ገዳም ተደፈረብን ብለው አበው ሲጮሁ፡ ያካባቢውም ህዝብ ሁሉ ተባብሮ ሲነሳ አንዲት ቃል አለመተንፈሳቸው የሚያያሳየን ገብረ ኪዳን ደስታና ስብሀት ነጋ ያዘጋጁት ወጥመድ ካመረታቸው ዋናዎች ውስጥ አንዱ መሆናቸውን ነው።

በበኩሌ ዛሬ የማደርገርውና የምጽፈው ነገር ሁሉ ሚዛኑን ከለቀቀ፡ ነገ እኔንም ከወጥመድ እንደሚከተኝ ይገባኛልና፤ ያቡነ ጳውሎስን ተጠማጅነትና አጥማጅነትን ለትንሽ ደቂቃ እዚህ ላይ ልግታና፡ ማህበረ ቅዱሳን ስለሚባለው ድርጅት ላንድ አፍታ የተረዳሁትን መግለጽ እፈልጋለሁ።

በመሰረቱ በወጣቶች ጉዳይ መምሪያና በሰበካ ጉባኤ መመሪያ በምሰራበት ጊዜ ወጣቱን አቅፈው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አጠቃላይ ጉባኤና ሃይማኖተ አበው የሚባሉ እንጅ ማህበረ ቅዱሳን የሚባል ድርጅት አልነበረም። የተቋቋመው እኔ ከወጣሁ በኋላ ስለሆነ በድርጅቱ ላይ የሚወራውን ክፉና ደግ በሩቅ ከመስማት በቀር የማውቀው ነገር የለኝም።

ይሁን እንጅ የማህበረ ቅዱሳን ወኪሎች ነን የሚሉ ሰዎች በከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባደረሱት ውዝግብና በከንሳስ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ላይ እስካሁን የሚያካህዱት የስም ማጥፋት ዘመቻ ከክርስትና እምነት ውጭ ስለሆነ ማህበሩ አውቆም ሆነ ሳያውቅ በገብረ ኪዳን ወጥመድ ውስጥ ገብቷል።

ምንም እንኳ በቀደሙ አባቶቻችን በነ አቡነ ባስልዮስ ተባርኮ በሊቃውንቱ በነ መላከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ትምርት እየተቀርጸ በመንቀሳቀስ ብዙ ያገለገለውን የሃይማኖተ አበውን ድርጅትና ሌሎችንም የሰንበት ትምህርት ቤቶችን እየደመሰሱ ባልተረዱት ነገረ መለኮትም እየገቡ ከቤተ ክርስቲያኒቱና ከሊቃውንቱ ጋራ በመጋጨት የተዘፈቁበት ቀውስ ቢያሳዝንም፤ በአካል ርቄ በቆየሁባቸው አመታት ለምወዳት፡ ላሳደገችኝና ላስተማረችኝ ቤተ ክርስቲያኔ ለዳረጉላት መላክም አገልግሎታቸው ምስጋናየን አልነፍግም።

<u>አቡነ ጳውሎስ ያፈኑትን በአሩሲ ስለታረዱት ክርስቲያኖች፡ በየጊዜው ጉዳት ስለ ሚደርሳባቸው ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ነቅተን እንድንጮህ በኢትዮጵያ ላለው ህዝብ ቃጭል፤ ተሰደን በሩቅ ለምንኖረው ደወል ሆነው የድረሱልን ጩኸት ያሰሙን የማህበረ ቅዱሳን ልጆች ናቸው። ስለ ገዳማቸው በመጮኽ ላይ ያሉትን አበው ባንድ ኩንታል ስኳር ዝም ለማሰኘት ከሞከሩት ከጎንደሩ ሊቀ ጳጳስ ከአቡነ ኤልሳዕ ይልቅ ማህበረ ቅዱሳኖች በዚህ ጉዳይ ባለውለታወቻችን ናቸው። ማህበሩ ይህን በማድረጉም አሁን ባለበት ወቅት በነ ፋሌቅ መከሰሱን ልንዘነጋው አይገባም። ስለነገረ መለኮቱ መዛባት ብዙ እየተጻፈና ሰው ሁሉ እየተገነዘበው ሳለ፡ ባልሰማ ባይነት እየጣሰ እስከ ማውገዝ ርቆ በመሄዱና ሌላውን እየጠለፈ በተጋዘበት ታሪኩ የሚደርስበት ወቀሳ ተገቢ ቢሆንም፤ የተዛባውን ነገረ መለኮት ያመነጨው ማህበሩ አይደለም። ማህበሩ ሌላውን እንዲያጠምድ ከወጥመድ የከተቱት እነ አቡነ ጳውሎስ ናቸው። ይህንንም ገልጾ አለመናገርና መወቀስ የሚገባበትን ስህተቱን ለይተን እየተናገርን ከመውቀስ ርቀን ባልፈጸመው ሁሉ በማህበሩ ላይ መዝመት እግዚአብሄር የሚቀበለው አይደለም። ቤተ ክርስቲያንንም መጉዳት ነው።</u>

ይሁን እንጅ ማህበሩ በኛ በከንሳስ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደሚያደረገው ካቅሙ በላይ በሆነ በነገረ መለኮት ውስጥ ዘሎመግባትና፤ ሰውን ሁሉ በየመንደሩ እየዞረ በየቤቱ እየገባ የሚፈጽመውን አሉባልታ ዘመቻ እንዲያቆም ሂስና ተግሳጽ በሚሰነዝርበት ላይ ሁሉ ኦርቶዶክስ አይደለም የሚለው ባህርይ ለጠቅላላው ቤተ ክርስቲያናችን ጠቃሚ አለመሆኑንና በመጨረሻም ለራሱ ለድርጅቱ ህልውና እጅግ የሚያሰጋ መሆኑን ሊረዳ ይገባዋል። የተሻለ ግንዛቤ አለኝ የሚል ሁሉ ማህበሩ <u>የተሰለፈበትን አገልግሎት በትእግስት በትህትናና በፍቅር እየቃኘ ቤተ ክርስቲያናችንም ከኦርቶዶክሳዊ ሚዛኗ እንዳትወጣ እየተጠነቀቀ እንዲቀጥል ማበረታት እንጅ፡ ከነ አቡነ ጳውሎስ ጋራ ተረባርቦ እነ ፋሌቅ በማህበሩ ላይ ያቀረቡበትን የጠለፋ ፖለቲካ እያስተጋቡ ማህበሩን እንዳለ ለመምታት መሞከር ክርስትና አይደለም።</u>

ይልቁንስ ማህበረ ቅዱሳንና ከማህበሩ ጋራ በመጋጨት ያላችሁ፡በውስጥና በውጭ ተበትነን በስደት ላይ ያለን ኢትዮጵያውያን ሁላችን በመተባበር ልናጤነው የሚገባ ነገር አለ። <u>"ከፖለቲካ ነጻ ናት፡ ሲኖዶስ</u>

የሚባል ነጻ ያስተዳደር መዋቅር አላት፡ መሪዋም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፖትርያርክ፡ የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀመንበር፤ የአኩስም ሊቀጳጳስ፤ የደብረ ሊባኖስ እጨጌና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሊቀመንበር ነው። የመንግስት እጅ ፈጽሞ አይነካትም›› እየተባለ በሚነገርላት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ **ገብረ ኪዳን ደስታ** አዋቅሮ ስብሀት ነጋ የዘረጋው የስለላ ወጥመድ፤ ይህ ሁሉ ግፍና በደል ከፈጸመ ፤ በአገር ውስጥ ባሉት የመንግስትና የግል ድርጅቶችማ እነ ስብሀት ነጋ ምን ያህል ተነግሮ የማያልቅ ደባ በመፈጸም ላይ እንዳሉ በመገንዘብ በነሱ ላይ ቁጣችንንና ኃይላችንን ልናስተባብር ይገባናል።

ተክቦ ተክቦ አቡነ ጳውሎስ ከተኮፈሱበት ከስልጣንና ከማዕረግ ስሞቻቸው አንዱ የስልጣን ካብ፤ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሊቀመንበርነት ነው። ሊቀመንበር ሊሆኑ የቻሉት፡ የዓለምን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ከቆረቆሩት አንዷ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያናችንን በመምራት ላይ ስላሉ ብቻ ነው። እነዚህ መስራች አባላት በሊቀ መንበርነት ጉባዔውን በየተራ ይመራሉ። በዚህ ፖሊሲ በዚህ ዘመን በመንበሩ ላይ ያለ ፓትርያርክ፡ እኛን ማለትም ጠቅላላ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምእመናንን ወክሎ በሚያደርገው ተልእኮው የሚፈጽመው እንጅ፤ እነ ፋሌቅ እንደሚሉት አቡነ ጳውሎስ በብጽእናቸው በቅድስናቸው በሙያቸው ተወዳድረው የገቡበት አይደለም። ይህን ባልተገነዘበው ህዝብ ህሊና ላይ ያቡነ ጳውሎስን ታላቅነት ለመጫን እነ ፋሌቅ ከተጠቀሙባቸው ወጥመዶቻቸው አንዱ ስለሆነ ይህም ከህዝብ ህሊና መፈንጠር ያለበት የህሊና ወጥመድ ነው።

አቡነ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ በተለያዩ መስመሮች አገልግሎት የሚሰጡትን የቤተ ክርስቲያን ልጆች እኩል በማያት በመካከላቸው የሚፈጠረውን ውዝግብ አርግበው አስማምተውና አስታርቀው በስህተት የገባውንም የነገረ-መለኮት ስህተት በሊቃውንት ጉባኤ እንዲታረም አርገው ውዝግቡን እንዳይነሳ ከመዝጋት ይልቅ: አሁንም ለሌላ ዘዴ ይጠቀሙበት ዘንድ አባ ሰረቀን ብቻ ታድገው ማህበረ ቅዱሳንን ለመምታት ያደረጉት እንደሆነ ሊሰውሩት የማይችሉት ገጠ የታየ ሸፍጥ ነው። ጉዳዩ ለይስሙላ ቀረበ ተባለ እንጅ በይፋ ደፍሮ የተነጋገረበት አካል የለም። ራሳቸው የፈጠሩት የሊቃውንት ጉባኤ የሚባለው ይህን ተነጋግሮ ለመወሰን አቅምና ችሎታ በራሱ ላይም እምነት ስለሌለው ተፈራርቶና እርስ በርስ ተያይቶ እንዲበተን አድርገውታል።

በዚህ ዘመን ካለው ሊቃውንት ጉባኤና ሲኖዶስ የቀና መመሪያ አገኛለሁ ብሎ ከመጠበቅ፡ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንና ለጠቅላላዋ አገራችን ቅድሚያ በመስጠት፡ ከድርጅት፤ ከግላዊ ስሜት፤ ካፈርኩ አይመለሰኝ ባይነትና ካቡነ ጳውሎስ ወጥመድ እራሳችንን ነጻ አድርገን፤ እውነት የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ልጆች ከሆን እጅግ ርቆ በመሄድ ከጀሆባ ዊትነሶች ከሞርሞኖችና ከአንሊ ጅሰሶች የሰማነውን ሁሉ እየነተትን ወደኛ በማምጣት ቤተ ክርስቲያናችንን የትግል ሜዳ ልናደርጋት አይገባም። እንኳን ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያናችን ትላንትና የተፈጠሩት ነገም የሚፈጠሩት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የየራሳቸው ያተረጓጎም ዘይቤ አላቸው። ይህ ባይኖር ኖሮ አንድ ቋንቋና አንድ ባህል ያላቸው ምዕራባውያን ክርስቲያኖች የተለየዩ አብያተ ክርስቲያናት ባልፈጠሩም ነበር።

ጎራ ላይተን መናኞች ቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ሲከፉቸው ያንጎረጎሩትን ሁሉ ተጽፎ በመገኘቱ ብቻ ለቅድስት ድንግል ማርያም እመቤታችንና ለነገረ መለኮት መለኪያ አድርገን በማቅረብ ቤተ ክርስቲያናችንን አናዋርዳት። በተለያዩ ድረ ገጾች እየተነበቡ ያሉት እውነት ተደርገው ከሆነ፤ እጅግ የሚያሳዝን ነው። ***መልክ*** እየተረጎመ ለማስተማር በመሞከር ቤተ ክርስቲያናችንን ያስነቀፈ ሰው እንደተከሰተ በስፋት ተነግሯል። እስካሁን በቤተ ክርስቲያናችን ተደርጎ የማይታወቅ ነው። የግዕዙን ያተረጓጎም ስልት ጠንቅቀው የተረዱ ሰዎች እንኳ አድርገውት የማያውቁትን፡ ሙሉ ችሎታና ብቃት

የሌለው ሰው ከዚህ ውስጥ ገብቶ የሚዘባርቅ ከሆነ በገብረ ኪዳን ወጥመድ የተያዝክ ነህና አቁም ልነለው ግዴታ አለብን።

ከዚህም ጋራ ለሰባት አመታት ተደጋግሞ ስለተጻፈው "ጥንተ አብሶ" ስለሚባለው ነገር ሰሞኑን እንደገና መጻፍ የጀመሩ ሰዎች አሉ። እኛ ሳንዳስሰው ያለፍነው ወይም የተሳሳትነው ካለ ብታርሙት መልካም በሆነ ነበር። ነገር ግን ነገሩን እያጓተቱ እንዳዲስ ለህዝብ በማቅረብ እርስ በርስ መጋጨትን ከመቀጠል ይልቅ፡ እነ አቡነ ጳውሎስ አንድ ሰው ሊታደጉ ሲሉ ያደረጉትን ደባ በማውገዝ ከዚህ ቀደመ ተብራርቶ በቀረበላቸው ሀሳብ ላይ በመነጋገር መንፈሳዊ ተልእኳቸውን እንዲፈጽሙ ተጽእኖ ማድረግ በተገባ ነበር። ከዚያም አልፎ እንዲያውም አባቶች "ወአናሚሁኒ መንፈስ ቅዱስ" በሚለው ሀረግ ላይ፡ የእመቤታችንንም ቀሪ ሰውነት መለኮት ተዋህዶት ነበር እንዳያሰኝ፡ ከመለኮታዊው ውህደት የእመቤታችን ቀሪ ሰውነት ለመለየት ሲሉ፡ የከፈለ ያነጻ ያዋሀደ መንፈስ ቅዱስ ነው ያሉትን "ስለሷ ሰውነት መንጻት ሳይሆን ከፍሎ የተወሀደውን ሥጋ ብቻ ነው ያነጻው" በማለት ካባቶቻችን አተረጓጎምና ከመላ አርቶዶክሱ ሚዛናዊ ግንዛቤ መውጣት ይመስለኛል። እባካችሁ እልክ ውስጥ በመግባት ሰው ወይም ድርጅት ለመጉዳት ሲባል ከአባቶች ግንዛቤ አንውጣ። ያለ ጥላቻና ስም መጠፋፋት በቅዱሳት መጻህፍት ያሉትን ነገሮች እያወሱ መነጋገሩ መልካም ቢሆንም፤ "ከመ ይኩኑነ መራህያነ ፍኖት ርትዕት ከመ ንርከብ ፍኖተ እንተ ትወስደነ ለገቢረ ሠናይ፡ ዘንትዌደስ ባቲ በደሀሪትነ ወከመ ይህንጹ ደኃሪትነ በሠናይ ሕንጻ ላዕለ መሠረት ጽኑዕ ዘኢያንቀለቅል፡እንተ ይእቲ ህንጻ መምህራን ትሩፋን ወባቲ ናጽንእ ሃይማኖተ ሕይወትነ"(ሃ.አ. ም. ፻፷ ቁ. ፭፫) ሲል የአንጾኪያው ኦርቶዶክሳዊው ዘካርያስ የሚባለው ሊቅ የተናገረውን አንዘንጋ።

አስተምህሮው ሳይገባችሁ ለተምታታባችሁ ሁሉ፡ የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምህሮ ለመረዳት በጎ ፈቃድ ካላችሁ በዚህ ጉዳይ እርስ በርስ ከመጣለፍ ወጥታችሁ የሊቃውንቱን አተረጓጎም ተረድታችሁ ለአገራቸውና ለእምነታችው ከልብ ከሚታገሉት ጋራ ትቆሙ ዘንድ፤ ከዚህ ቀደም ላቡነ ማትያስ ጽፈን በላክንላቸው ከዚህ በታች ፩ እስከ ፬ የገለጽናቸውን አሳቻ ጥቅሶች ልከንላችኋል። የምታደርሱበት መንገድ ካላችሁም አርሞ ማስተካከል አቅም አጥቶ ለተበተነው ሊቃውንት ጉባኤም ይረዳው ዘንድ አቀብሉልን። በጉባኤ ላልዋሉ ሰዎች እጅግ አስቸጋሪ ጥቅሶች ከዚህ በታች እነሆ!

፬ኛ. በዘመናችን ለመተርጎም አስቸጋሪ የሆኑ ጥቅሶች

እነዚህ ከ፱ እስከ ፴ ከዚህ በታች የገለጽናቸው አሳቻ ጥቅሶች በነገረ መለኮት ትምህርት በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ያልበሰሉትን ሰዎች በቀላሉ የሚያሳስቱ ጥቅሶች ናቸው። ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባቶች የመጻህፍቱ ባለቤቶች ሊቃውንት አበው ሀሳብ ሳይርቁ፡ የግእዙን ዓበይት አገባቦች እንደምልክት በመጠቀም አረፍተ ነገሮች የተሸከሙትን ጽንሰ ሀሳብ እየቀመሩ እንዲህ ይተረጉሟቸዋል።

ሀ. “ወሶበ ርእየ ንጽህናኪ” ይህን ያሉት አባ ህርያቆስ ናቸው። አባ ህርያቆስ ቅዳሴ ማርያም በተባለው ድርሰታቸው ይህን ያሉበት ምክንያት፤ ከቁጥር ፴፰ እስከ ቁጥር ፵፩ ድረስ “አኮ” በምትለው አፍራሽ አገባብና እና “አላ” በምትለው አስረጅ አገባብ ሰባት ጊዜ የገለጿቸውን የድንግልን ሰባዊ ሁለንተና ገብርኤል ማየቱን ለመግለጽ “ወሶበ ርእየ ንጽህናኪ” የምትለዋን ሀረግ ተናገሩ እንጅ፡ እመቤታችን ያለ ጥንተ አብሶ ተጸንሳ ተወለደች ለማለት አይደለም።

ለ. “ኢያዕመረ ዮሴፍ እስመ ዘተፈጥረት እምነ ጽቡር ጽሩይ ትከውን መቅደሶ ለዕግዚአብሄር”(ሃይ ምዕ ፶፰ ቁጥ ፴፩) ያለው ኤራቅሊስ ነው። ይህን ያለበትም ምክንያት ከቁጥር፳፱ ጀምሮ “ወሶበ ሰምአ ዘንተ ዮሴፍ ሰገደ ለድንግል ወገነየ ለንጽህናሃ ወአእመረ ከመ ይእቲ ድግል” እስከ ሚለው እስከ ቁጥር ፴፩ ድረስ፤ ስምንት ጊዜ ኢያእመረ እያለ በዮሴፍ ህሊና ላይ ስለተከሰቱት ተቃራኒ ነገሮች ሲናገር ቆይቶ፤ ዮሴፍ ነገሩን አውቆና ተረድቶ ህሊናው ተረጋግቶ የእመቤታችንን አጸናነስ እሱ ከጠበቀው ባላይ ሆኖ ስላገኘው “ሰገደ ለድንግል ወገነየ ለንጽህናሃ” ብሎ ተናገረ። ጽንሱ በእመቤታችን ማህጸን ዮሴፍ በጠበቀው መንገድ ሊከናወን ይቅርና፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት ስለተፈጠረች፡ ከተፈጠረች ጀምሮ ዮሴፍ ከጠረጠበት ነገር ፈጽማ የራቀች መሆኗን የተረዳውንና ያወቀውን ኢዕመረ ብሎ ገለጸው። ኤራቅሊስ እመቤታችን ያለ ጥንተ አብሶ ተወለደች ለማለት ይህን አረፍተ ነገር ፈጽሞ አልተናገረውም። ይህም ማለት ልክ አባ ህርያቆስ ሰባት ጊዜ በ“አኮ” አፍራሽነትና በ “አላ” ገንቢነት ወይም አስረጅነት ስለድንግልናዋ ለተናገሯቸው ሀሳቦች “ወሶበ ርእየ ንጽህናኪ” እንዳሉት፤ ኤራቅሊስም ስምንት ጊዜ ኢያእመረ እያለ የደረደራቸውን አፍራሽ ሀሳቦች ኢዕመረ በማለት ሀሳቡን ደመደመ።

ሐ. “ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘ ፈጠራ” ያለውም ቴዎድጦስ የተባለው ሊቅ ነው። ቴዎድጦስ ይህን ያለበት ምክንያት በምዕራፍ ፶፫ ከቁጥር ፫ ጀምሮ “ወነበረት ድንግል በድንግልናሃ ከመ ቀዳሚ ወኮነት እመ ወዘያማስን ሕይወተ ኢገብረ ሙስና ወዘይሁብ ህይወተ ኢያማሰነ ወኢምንተኒ” እያለ የገለጸውን፤ ማለትም እመቤታችን በሰውነቷ ምንም እንዳላደረግችና ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ ዘላለማዊት ድንግል መሆኗን፤ የወንድ ዘር ለድንግል ማህጸን ርኩስ መሆኑን እየገለጽ የመጣውን ሀሳብ በቁጥር፳፪ ላይ “ወተወልደ እምህላዌየ በመንክር ግብር ወተወክፈ ልደተ ከማየ በመንክር ግብር እንዘ ውእቱ እግዚአብሄር ቃል ወሰመያ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲቶ ወጺአ እምከርሳ እንዘ ድንግል ይእቲ” ብሎ ለመደምደመው ሀሳብ “ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘ ፈጠራ” አለ እንጅ፤ እመቤታችን ያለ ጥንተ አብሶ ተወለደች ለማለት አይደለም። ይህ ዘመን ያፈራቸው መምህራን “ወኢረኩሰት በምንትኒ” የምትለዋን ሐረግ በመቆንጸል ጥንተ አብሶንም ያጠቃልላል በሚል ሽባ ግምታቸው፤ ያለ ጥንተ አብሶ ተወለደች ይላሉ። ሊቃውንት ቅድስት ድንግል እመቤታችን ጌታችንን ያለወንድ ዘር ወለደችው ለማለት፤ እንበለ ርኩስ፡ እንበለ ኃጢአት፡እንበለ ስእበት፡ እያሉ ይገልጹታል።

ለምሳሌ፡-

“እስመ እንበለ ርኩስ አዳም ዳግማዊ ይትፈጠር”(ሃይማኖተ አበው ፶፰፡፴፭)

“ዘወጽአ እም ሕላዌነ ዘእንበ ኃጢአት ባህቲታ”(ሃይማኖተ አበው ፶፯፡፮)

“ወአጽንአ ቦቱ ትስብእተ ዚአነ ዘእንበለ ኃጢአት”(ሃይማኖተ አበው ፯፡፳፭) የሚሉትን ሀረጎች ሁሉ “ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ” በማለት ሰው ከተወለደ በኋላ የሚፈጽመውን ሁሉ ስህተት እንዳልሰራ ቢያጠቃልልም፤ መሰረታዊው ትርጓሜው ያለወንድ ዘር ተወለደ ነው።

ርኩስ የምትለዋ ቃል ለወንድ ዘር በቅጽልነት በመግባቷ ባንድምታው ትርጉም የቃሏን ማህጸን ማስፋት ላልመደ አዕምሮ መቀበል ቢያስቸግርም። ያለቦታው ለሚገኝ ነገር የሚሰጥ ቅጽል ነው።

በሊቃውንት አተረጓጎም የወንድ ዘር ርኩስ፡ ስእበት (ኃጢያት) የሚባለው ያለ ወንድ ዘር ክርስቶስ ለተጸነሰበት ለእመቤታችን ማህጸን የወንድ ዘር አስፈላጊ አለመሆኑን ለመግለጽ ነው። ቅድስት እመቤታችን በተቀደሰው በኢያቄም ዘር ለተጸነሰችበት ለሀና ቅድስት ማህጸን ተገቢውና ተስማሚው ስለሆነ ቅዱስ እንጅ ርኩስ አይደለም። (አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተጸነስኪ፡ አለ በሩካቤ ሥጋ እም ሐና ወኤያቄም ተወለድኪ" ብሎታል። በተቀደስ ጋብቻ ጽንስ ለሚከናውንበት ማህጸን ሁሉ የወንድ ዘር ስእበት ወይም ርኩስ አይደለም። እንዲያውም ቅዱስና "ፈልፈለ ሕይወት" ይባላል።

የወንድ ዘር ለእመቤታችን ማህጸን ርኩስ የሚባለው፤ አሳማውን አይጡን አህያውን ርኩሳን እንደምንላቸው ማለት ነው። እኛ ርኩሳን የምንላቸው እንስሳት ሁሉ ለምግብነት ከሚያገለግሉን ከምንበላቸው እንስሳት የተለዩ ናቸው ለማለት እንጅ፤ ባህላቸው ፈቅዶላቸው፡ ፍላጎታቸውም ተቀብሎት፡ ለሚበሏቸው ሰዎች፡ርኩሳን አይደሉም። ለፈጠራቸውና ለተፈጠሩለት ዓላማም ቅዱሳን ናቸው።

እንደዚህም ሁሉ ክርስቶስ ፱ ወራት የቆየባትን የድንግል ማህጸንን ከሄዋንና ከናቷ ከሐና ማሕጸን ልዩ ያደረጋት ቅዱስ ኤፍሬም "ከርሥ ዘፈትሐ ላዕሌሃ ትለድ በጻእር ወህማም ወኮነት ፈልፈለ ህይወት ወወለደት ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ" እንዳለው በሩካቤ በዘር በጻእርና በጋር እንድትወልድ ከተፈረደባት ከሴቶቹ ሁሉ ማህጸን የቅድስት ድንግልን ማህጸን ለመለየት እንደሆነ ልንገነዝብ ይገባል። ከዚህ ሁሉ ሀተታ የገባሁት "ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘ ፈጠራ" የምትለዋን ሀረግ ከዚህ ውስጥ በመቀርቀር ለተሳሳተ ግንዛቤያቸው ማስረጃ እያደረጉ በመጥቀሳቸው ነው።

መ. ቅዱስ ኤፍሬምም ቢሆን በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ ንእድ፡ክብት፡ ቅድስት እና ቅድስተቅዱሳን እያለ በተናገረበት አንቀጽ ሁሉ "እስመ ኮንኪ ማህደሮ ለልዑል" እና "እስመ ኮንኪ ድሉተ ለተወክፎ ቃለ አብ" እያለ ለተናገራቸው ማብራሪያዎቹ እስመ በምትባለው ዓቢይ አገባብ አስረጅነት ለደመደማቸው ትንታኔዎቹ እንጅ፤ ያለ ጥንተ አብሶ ስለተወለድሽ ብሎ ባንድም ቦታ አልተናገረም። በነዚህ ሁሉ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ትንታኔና ህሊና ውስጥ ያልነበረ ነገር እየጨመሩ መናገር የመጨረሻ የመጨረሻ የመጨረሻ በደልና ኃጢያት ነው። ይልቁንስ ጥንተ አብሶ ማለት ሊቃውንቱ ያላሉትን በነሱ ስም ይህን የመሳሰሉ ነገሮችን እየፈጠሩና እነሱ የተናገሩትን ገጸ ንባብ እያጣመሙ ማቅረብ ነው።

ይህ ጥንተ አብሶ የተባለውን ነገር ከሮማ ካቶሊክ ግንዛቤም ሆነ፡ ከሂንዱኢዝም ጋራ እያገናኙ ወይም ያቴቴ ጨሌ አስተሳሰብ የመሰለ ሀሳብ ከእመቤታችን ጋራ በማገናኘት መነገሩ ከኦርቶዶክስ ትምህርትና እምነት ፈጽሞ የራቀ ነው። እንኳን ለኛ "ጥንተ አብሶ" የሚባለውን ነገር በአዋጅ ለተቀበለችው ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ከጊዜ በኋላ የጨመሩት እንግዳ ትምህርት ነው" ብለን ለነ አቡነ ማትያስ ብንነግራቸውም ለመረዳት ካቅማቸው በላይ ስለሆነ፤ ይረዳቸው እንደሁ ብለን በመገመት ከዚህ በታች ያሰፈርናቸውንም ታሪካውያን ማስረጃወች ጨምረን ልከንላቸው ነበር።

- ፭ኛ በ390 በአውግስቲንና በቅዱስ ዮሀንስ አፈወርቅ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት አውግስቲን አመንጭቶት፤ ቅዱስ ዮሀንስ አፈወርቅ መታው
- ፪ኛ እንደገና ስር ሰዶ በሮማ ካቶሊኮች በ1274 ብቅ ባለበት ዘመንም ቶማስ አኪኖስ መታው።

- ፱ኛ በ1854 ባንዲት መበለት ህልም ላይ መስርታ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም በአዋጅ ተቀበለችው።
- ፩ኛ ወደኛ ቤተ ክርስቲያንም የዘመኑ የፖለቲካ ወጥመድ ጠልፎ ከጣላቸው ብዙዎች አንዱ የሆኑት አለቃ አያሌው ከመጋቢ ብሉይ ሰይፈ ጋራ በነበራቸው ግላዊ ጸብ ብቻ በ፲፱፻፹፩ አመተ ምህረት በእልክ ከተቱት።

እኛ ጊዜያችንን አጥፍተንና ደክመን ከላይ የገለጽናቸውን ጽፈን የላክንላቸውን አቡነ ማትያስ ሳይመለከቱ፡ ወይም ደብቀው፤ አግኝለሁ በሚል መንፈስ ሌላ እራሳቸው የጠለሰሙትን የስህተትና የክህደት ጠልሰም ከኪሳቸው አውጥተው አነበቡ።'' የኦርቶዶክሱን ትምህርትና እምነት ጽፋችሁ ላኩልኝ ባሉን መሰረት ጽፈን የላክንለዎን ወዴት ደብቀው ነው ይህን የሚያነቡት? ላንላቸው፡ የሰጡን መልስ ''የላካችሁልኝ ጽፈቱ ደቃቃ ስለሆነ ላነበው አልቻልኩም'' የሚል የዋሁን ህዝብ የሚያደናግር ሸፍጥ የተሞላበት መልስ ሰጡ።

ሸፍጥ የምንለውም፡ በኪሳቸው ተሸክመው የመጡት ጠልሰም እኛ ከላክንላቸው እጅግ ረቂቅ ነበር። ይህን ሁሉ ካደረጉ በኋላም ሰልችተንና ተቀይመን እሳቸውን ለመርዳት መሞከራችንን አላቆምንም። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለሰጧቸው ቸርነት በተቀበሉት የሊቀ ጵጵስና መስመር ላይ ከመድረሳቸው በፊት አዘውትረው ሲቀድሱት በነበረው ሰሞነኝነት ሙያቸው አስተምህሮውን ለማስረዳት ''ህብስት በጻህል ወይን በጽዋዕ ሳይዘጋጅ ቅዳሴ እንደሌለ ሁሉ፡ እመቤታችንም ወደ መኖር ሳትመጣ በላነበረችበት ጊዜ ነጻች ተቀደሰች አይባልም'' በማለት ነገርናቸው። እንዲረዱት የተደረገላቸውንም ሙከራ እንደ ድካም በመቁጠር፡ የኦርቶዶክሱንም ነገረ መለኮት ሰምተውት ባለማወቃቸውም ጭምር፤ ጭራሽ ባሰባቸውና ''የመናፍቃን ነው'' ብለው ራሳቸውን ጨርሶ ገደል የከተታቸውን 12 ገጾች የያዘች ጠልሰም መሳይ ጽሑፍ በተኑ። ''እረ አባታችን እጅግ ተሳስተው ወደቁ፡ ይህ የሚያደርጉት ነገር ወደ አዋቂዎች በደረሰ ጊዜ ራሰዎን ያዋርደወታል'' ቢባሉም ''ብትፈልጉ ወደ ሰማይ ተኩሱት'' የሚል ትዕግስት አስጨራሽ ትዝህርት የተመላበት መልስ ሰጡን። ይህ ትእግስት አስጨራሽ መልሳቸውም እነ ፕሮፌሰር ዲያቆን አስራትን እያነቀ የገደላቸውን እነ አለቃን ጠልፎ የጣላቸውን መስገርት የሚገልጹ በተለያዩ ርእሶች ተጽፈው በሰፊው የተነበቡት አሁንም በድረ ገጻችን ተደርድረው በመነበብ ላይ ያሉት ወጥመድ አስፈንጣሪ ጦማሮች ፈለቁ። (ዝርዝሩን ለማንበብ http://www.medhanialemeotcks.org/ ድረ-ገጽ እዚህ ላይ ይመልከቱ:)

በተከታታይ ተዘጋጅተው በመቅረብ በሰፊው የተነበቡት እነዚህ ጦማሮች አገራችንና ቤተ ክርስቲያናችን ያሉበትን ክፉ ዘመን መግለጽ ብቻ ሳይሆን፤ እኛም እንደ ቀደሙ ጀግኖችና ሊቃውንት አበው አባቶቻችን የነቃን እንድንሆን የሚያሳስቡ ናቸው።

፭ኛ. ግራ ቀኝ የሚያዩ ሩቅ የሚያስቡ ወጥመድ አስፈንጣሪ ቆቆች እንደነበሩት አባቶች እንሁን

ጦማሮች የፈለቁበት ምክንያት ለጊዜው እጅግ ያሳዘነንና ያበሳጨን ቢሆንም፡ ያሰለፍነውን ውጣ ውረድ የተደረገብንን ዘመቻ ተቋቁመን ሳንበታተን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከተዘረጉት ወጥመዶች አንዷን ማስፈንጠር እንድንችል ጽናቱን የሰጠንን አምላክ እናመሰግናለን። የተዘረጋውን ወጥመድ ከፊታችን በማስፈንጠር ሳንገታ፡ ከስሩ ተነቅሎ እንዲወድቅ ባደረግነውን ያላሰለሰ ጥረታችን የፈለቁትን ጦማሮችና ከወገኖቻችንም ያገኘነውን ድግፋ ዘወር ብለን ስንመከታቸው ወንጌላዊው ሉቃስ ለቴዎፍሎስ ወንጌሉን ሲጽፍ፡ እንደመግቢያ የተጠቀመበትን ሀረግ እያስታወስን ደስታችን ፍጹም ሆኗል።

ሉቃስ ለቴዎፍሎስ ወንጌሉን ሊጽፍ ሲጀምር፤ እሱ በነበረበት ዘመንና ከሱ በፊት የነበሩት ሰዎች ጀምረውት እንደነበረ ትዝ ብሎት "እስመ ብዙሀን እለ ወጠኑ ይንግሩ ወይምሀሩ በእንተ ግብር ዘአምኑ፡ በከመ መሀሩነ እለ ቀደሙነ ርእዮቶ፡ ሊተኒ ረትአኒ እትልዎ እምጥንቱ ወጥዩቀ ኩሎ በበመትልው እጽሕፍ ለከ" (ሉቃ ፩፡፩_፫) ብሎ ነበር። ይህ ማለት፡ ከመጀመሪያ አንስቶ የዐይን ምስክሮች የመልእክቱ አገልጋዮች ያስተላለፉት ነው። እኔም በዘመኔ ከመሰረቱ በጥንቃቄ የታሪኩን ቅደም ተከተል በጠበቀ ሁኔታ እንድጽፍልህ ቀናኝ" ብሎ ለቴዎፍሎስ ነገረው። እኛም በዘመናችን የተከሰተውን ነገር ከየት ተነስቶ እኛ ዘንድ እንዴት እንደደረሰ፤ የታሪኩን ቅደም ተከተል እና ያባቶቻችንን ያተረጓጎም መንገድ በመከተል በተብራራ ሁኔታ በማቅረብ በዚህ ወጥመድ ለተያዙት ሁሉ እንድናቀርበው ቀናን።

ባለማስተዋል ለነፋሌቅ ወጥመድ ጅግራ የሆናችሁ ሁሉ አስቡ!። ከጅግራው የባሰ ዛቀኛ በሬ የሆናችሁ ሁሉ በፊታችሁ የተደቀነውን ገደል ተመልከቱ። "በሬ ሆይ! ገደል ትገባለህ ግብስብስ ስታይ" የሚባለውንም ያባቶችን ማስጠንቀቂያ አትርሱ። እንደ ቆቋ ነቅተን በእምነት፡ በጸሎት፡በፍቅር፡ በሞራልና በተስፋ ላይ እንቅስቃሴያችንን መስርተን ትግላችንን ከቀጠልን፡ የሲኦል ልጆች አያሸንፉንም! ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፤ "የሰላም አምላክ የወጥመዱን አጥማጆች ከእግራችን በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጣቸዋል።(ሮሜ ፲፮፡፳) አርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ፊላታወስም "ወሰበረ ኖኃተ ብርት ወቀጥቀጠ መናስግተ ዘጎጺን" (ሃ ም ፻፬፡፬) እንዳሉት፡ የተጠመድንባቸው የብረት ወጥመዶች ይሰባበራሉ። የወህኒ ቤቶች ማሸጊያ ቁልፎችም ይንከታከታሉ።

የአባቶቻችን አምላክ የቆቋን ንቃት፡ አርቆ ማየቷንና ማሰቢን ያድለን!

ይቆየን

ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::

http://www.medhanialemeotcks.org/